በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ - 1


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሐምሌ ፲ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

## የትምህርቱ ዓላማ

- ይህን ትምህርት በሁለት ክፍል በመክፈል በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባውን ኦርቶክሳዊ እይታ እንመለከታለን፡፡

## *መንፈሳዊ ሕይወታችን ደካማ ነውን?*

- ምናልባትም የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚጠይቁ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
    - ክርስቲያን ነኝ ነገር ግን ሰላሜን አጥቼዋለሁ…
    - መንፈሳዊ ሕይወቴ አንዳንዴ ቢሻሻልም ተመልሼ ደግሞ ተዳክሜ እገኛለሁ…
    - መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት እጅግ ያስቸግረኛል፡፡
    - ጸሎቴ እጅግ ጥቂትና ሊሰማ የማይችል ደካማም ነው…
    - ኃጢአት እሰራለሁ፣ ንስሐ እገባለሁ፣ ተመልሼም በኃጢአት እወድቃለሁ…
    - በዚህ ደካማ ሕይወት የምኖረው እስከ መቼ ነው?
    - ንጹሕ ክርስቲያናዊ ሕይወትን መምራት የምችለው እንዴት ነው?
    - ኃጢአትን በማሸነፍ ቃል የገባልኝን የአምላኬን የክስርቶስን ሰላም እንዴት ልጎናጸፈው እችላላሁ?

# በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

- ለጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚሆነው በመንፈስቅዱስ መሪነት እግዚአብሔር በእኛ መኖሩ ነው፡፡ በደካማ ማንነታችንን ራሳችን የምንቆጣጠር አድርገን ካሰብን ከነደካማነታችን በመኖር እንቀጥላለን፡፡ *የሐዋ 4፡12፡፡*
- ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ሊኖረን የሚገባው የተቀደሰ ሕይወት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግኑኝነትና ኅብረት ነው፡፡
- የክርስቲያናዊ ሕይወት ዋና ዓላማው ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግኑኝነት መመሥረት ነው፡፡ ግኑኝነቱ ካለ ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸው ምልክቶች እንደሚከተለው እንደተነገረው ይገኙብናል፡፡
  - ‹‹በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ፡፡ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም፡፡ እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፡፡ … በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል፡፡ … አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ፡፡ … ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ፡፡ … እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት፡፡» *ዮሐ 15፡1-12፡፡*
  - «እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፡፡» *ገላ 2፡20፡፡*
  - ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፡፡» *ቆላ 3፡3፡፡*
- የእግዚአብሔር ልጆች የምንባለው በተስተካከለ በክርስቲያናዊ ሕይወት ስንኖር ነው፡፡

# <u>በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ</u>

- በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ፡፡

1. *<u>ፍጥረታዊው (ክርስቲያን/ኦርቶዶክሳዊ ያልሆነ ሰው)</u>*

- ይህን ዓይነት ሰው አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡›› *<u>ቀዳ ቆሮ 2፡14፡፡</u>*
- እንዲህ ያለውን ሰው አስመልክቶ ቀለል ያለ ሥዕል መሳል እንችላለን፡፡
- ፍጥረታዊው ሰው ሕይወትን በሚቆጣጠርበት ወንበር ራሱ ተቀምጦ ይገኛል፡፡
- ፍጥረታዊው ሰው እግዚአብሔር አምላካችንን ከሕይወት ክብ (ክልል) ውጪ ያደርገዋል፡፡
- የፍጥረታዊው ሰው ፍላጎቶች ሁሉ ራስ ወዳድነቱን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡
- ይህን ሕይወት የሚመራው ሰው ወንድሙ አቤልን እንደገደለው እንደ ቃየን ባለ ሕይወት በራስ ወዳድነት በተለከፈ የኃጢአት ሕይወት ይጓዛል፡፡ *<u>ዘፍጥ 4፡፡</u>*
- ይህን ሕይወት የሚመራ ሰው ብኩርናውን በምስር ወጥ እንደሸጠ እንደ ዓሳው ባለ ሕይወት ከበረከትና ከተሟላ ሕይወት ተለይቶ ይኖራል፡፡

# በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

## 2. *በስም ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳዊ) ተብሎ የሚጠራው ሰው*

- *እንዲህ ያለው ሰው ሕይወቱ በሥጋ ፈቃዱና በመሻቱ ብቻ የሚመራ ነው፡፡ ሥጋና መሻቱ ሕይወትን በሚቆጣጠረው ወንበር ላይ ተቀምጠው፣ ሕይወቱን ሳይቆጣጠር፣ ከሥጋው በመነጨ መሻት ብቻ መላ ትኩረቱ እየተሳበ ይኖራል፡፡*
- *እንዲህ ያለው ሰው የስም ኦርቶዶክሳዊ (ክርስቲያን) ነው፡፡ በሕይወትም የሚኖረው በድህነቱ ያገኘውን ጥቂት ሀብት ለሥጋ ፍላጎቱ ለማሟላት ብቻ ይመስለዋል፡፡*
- *እግዚአብሔር በሕይወቱ ስለመኖሩ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዱ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበቡ፣ መጸለዩ ሁሉ አስፈላጊ አይመስለውም፡፡ ‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፡፡» **ማቴ 15፡8፡፡** የሚለው እንዲፈጸምበት ምክንያት ይሆናል፡፡*
- *እንዲህ ያለ ሰው ለመንፈሳዊ ጉዳዮች አትኩሮት የሌለው በመሆን አምላካችን እግዚአብሔርንም ሌሎች ሊያስቡት፣ ሊያመልኩትና ሊታዘዙት የሚገባና እርሱን የማይመለከተው አድርጎ ይቆጥራል፡፡*
- *«እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም፡፡ ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም፡፡ ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?» **ቀዳ ቆሮ 3፡1-3፡፡***

# በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

## 2. *በስም ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳዊ) ተብሎ የሚጠራው ሰው…*

- እንዲህ ያለው ሰው መንፈስቅዱስ በሕይወቱ እንዲሠራ፣ ልቡንም እንዲለውጥለት፣ አንጽቶም ወደ እውነተኛ ኦርቶዶክሳዊነት (ክርስቲያንነት) እንዲለውጠውና መልካም ፍሬንም ለማፍራት እንዲያበቃው ከፈቀደ ወደ መንፈሳዊነት ሊቀየር መቻሉ መልካም ዜና ነው፡፡
- እንዲህ ያለው ሰው ፍላጎቱን ለማሟላት በራሱ ይመካል፡፡ ምክንያቶቹም፡-
  - የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅር ባይነት መርሳቱ ነው፡፡ «ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፡፡» ***ሮሜ 5፡8፡፡***
  - በቅዱስ ሉቃስ የተናገረውን የእግዚአብሔርን ኃይል መርሳቱ (መዘንጋቱ) ነው፡፡ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፡፡» ***የሐዋ 1፡8፡፡***
- በውጤቱም እንዲህ ያለው ኢክርስቲያናዊ ሰው የእግዚአብሔርን ኃይል ስለማይጠቀም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ደካማ ነው፤ ራሱን መረዳት ይቸግረዋል፣ ትክክለኛ ነገርን ለማድረግ ጊዜ ይወስድበታል ቢሠራም ብዙውን ጊዜ አይሳካለትም፡፡ «የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም፡፡» ***ሮሜ 7፡15፡፡***
- እንዲህ ያሉ ሰዎች ውስጣዊ ሕይወት ብንመረምር የሚከተሉትን እናገኛለን፡-
  - አለማመንን… ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዝን… ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰዎች ፍቅር ማጣትን… አለመጸለይን… የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ አለመፈለግን፡፡

# በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ሊኖረን የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ እይታ

***በስም ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳዊ) ተብሎ የሚጠራው ሰው…***

- እንዲህ ያሉ ሰዎችን ውስጣቸውን ብንመረምር የሚከተሉትን እናገኛለን፡-
  - ንጹሕ ያልሆነ አስተሳሰብን… *ሥጋዊ ቅንዓትን*… ክፋትን… ተስፋ መቁረጥን… በነገሮች ሁሉ ጽንፈኝነትን… መናደድን… ግብ አልባ መሆንን…
  - እነዚህ አስቸጋሪ የሆነ ደስታ የሌለበት ሕይወት ይመራሉ… በደከመ ሕይወት እያሰቡ በክርስቲያናዊ ሕይወት ከሚገኝ ኃይል ደህይተው ራሳቸውን ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳዊ) አድርገው ይቆጥራሉ … «በብርሃን (በእውነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት) አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ (በተሳሳተ ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚኖር) እስከ አሁን በጨለማ አለ፡፡» ***ቀዳ ዮሐ 2፡9፡፡***

***መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ፡-*** ታናሹ ልጅ የአባቱን ቤት ትቶ የሥጋ ፍላጎቱን የሚያሟላትን ሕይወት ተከትሎ ከሄደ በኋላ ተራበ፡፡ የተራበበትም ምክንያቱም ኃይልና በረከት ከሚያገኝበት መራቁ ነበር፣ አባቱ ብዙ ገንዘብ ስላጠራቀመለት በእጁ በሚገኘው ገንዘቡ ብዛት በስንፍና የሚመካው ሰውና፣ በራሱ ተመክቶ «ሁሉ ቢክዱህ እኔ ግን አልክድህም እንዳለ…» ጴጥሮስ ይጠቀሳሉ፡፡

***ምን ተማርን***

- ክርስትና በዓለም በምንመራው የዘወትር ሕይወታችን በአስተሳሰባችን፣ በምርጫችን መገለጥ የሚኖርበት መሆኑን፡፡ ***ገላ 2፡20፡፡***
- ፍጥረታዊው ሰው እጅግ ደካማና የኃጢአት ሕይወት እየመራ የሚኖር መሆኑን፡፡
- በስም ክርስቲያን(ኦርቶዶክሳውያን) የሆኑ በሕይወታቸው የሚታይባቸው ነገር ተለዋዋጭ እንደሆነና በክርስቲያናዊ ሕይወት የሚገኘውን ደስታ እንደማያገኙ፡፡

# ቀኖና ምንድን ነው?

***መልስ***

- *ቀኖና ከግሪክ የተወሰደ ቃል ሲሆን ትርጉሙም መሥፈርት ወይም መለኪያ ማለት ነው፡፡ ይህ መሥፈርት ወይም መለኪያ ተለይቶ መታወቂያ መንገድ አለው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቁመት የሚለካው በረጅም ወይስ በአጭር ሰው ክንድ ነው ብለን እንደሚያምታታን ያለ አይደለም፡*
- *ቀኖና በብቸኝነት የተሠራው ወይም የተሰጠው ለሰው ነው፡፡ ሌሎች ፍጥረታት ግን ሳያውቁት በተፈጥሮአቸው ታዘው ይሠሩታል፡፡*
- *ቀኖና ልክ ነው ወይም አይደለም … ተብሎ ተለክቶ ወይም ተመዝኖ በቤተ ክርስቲያን ይሰጣል፤ በገዳም እንዳለ መቁነን!*
- *በቤተ ክርስቲያን የሚያጠፋ የሚቀጣበት የሚሠራ የሚሸለምበት መለኪያ መሥፈርት አለ፤ እርሱም ቀኖና ነው፡፡*
- *ሰው መንፈሳዊ በሥራው ቅዱስ መሆን አለመሆኑ የሚለካበት ወይም የሚሠፈርበት መጠን ወይም ልክ አለው፤ እርሱም ቀኖና ነው፡፡ ብልጣሶር «በሚዛን ተመዘንህ፥ ቀልለህም ተገኘህ ማለት ነው፡፡…» እንደተባለ፡፡ __ዳን 5፡25፡፡__*
- *የቀኖና ሕግ ማለት የመሥፈሪያ ሕግ ማለት ነው፡፡ የዕውቀት ሁሉ ፍጻሜ ሕግ ነው፡፡ ጎበዝ ሾፌር የሚባለው የመንገድ ሕጎችንና የማሽከርከር ስልትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ ይህም እንኳን ለክርስቲያኖች በምድር ለሚከናወኑም ነገሮች ሕግ ያስፈልጋቸዋል፡፡*
- *ሁለት ሰዎችና አንድ ወንበር ብቻ ካለበት ሥፍራ ማን እንደሚቀመጥ ማን እንደሚቆም የምንወስንበት ሕግ (ሥርዓት) ያስፈልጋል፡፡ ጌታችን ያስተማረንን ትምህርት ጠብቀን እየፈጸምን የምንራመድበት ሥርዓት (ሕግ) ቀኖና ነው፡፡*
- *ሰው አደገ ሠለጠነ የሚባለው የሚመራበት/የሚመራበት ሕግ ሲኖረውና ሲመራበት ነው፡፡ የሥልጣኔ ውበት/ውጤት ወይም መጨረሻው ሕግ ነው፡፡ በዓለም ያደጉ የሚባሉት «አደጉ» የተባሉት ሕግ ስላላቸውና ስለሚመሩበትም ነው፡፡ የሰው ትራፊክ በሌለበት የሚቆጣጠር መሣሪያ እየተከታተለው አጥፊው ይቀጣል፡፡ መሠልጠን መገራት ማለት እንዲህ ነው፡፡ ኦርቶዶክሳውያንንም የሚገራንና የሚያሠለጥነን ሕግ ቀኖና ይባላል፡፡*

*__መልስ__*

# ቀኖና ምንድን ነው?

- «ያልተገራ ወይም ያልሠለጠነ ፈረስ የጌታውን ጥርስ ይሰብራል» እንደተባለው ያልተገራ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው፤ የተገራ ፈረስ ካልተገራው ይለያል፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን መማር፣ ትምህርተ ሃይማኖትን ማጥናት ማወቅ ማለት፤ አምላካችን ጌታችን ራሱን ምሳሌ አድርጎ ያስተማራቸው ሐዋርያቱ በግብር እንደመሰሉት ሁሉ በኦርቶዶክሳዊ ቀኖና ተቀርጾ ሥርዓት አክብሮ ፈጽሞ መገኘት ማለት ነው፡፡
- የቀኖና ቤተ ክርስቲያን መኖር ምክንያቱ ልዩነትን ለመፍታት(በአንድነት ለመኖር)፣ አንድነትን ለማጽናት፣ መብታችንን ለማስከበር (ወንዶች ፣ ሴቶችም የሚቆሙበትን ሥፍራ የደነገገላቸው ቀኖና ሕግ ነው)፣ ኦርቶዶክሳዊ ኃላፊነታችንንም እንድንወጣ ለማስገደድ ነው (ካህናትን ምዕመናንን የሚመሩበትን ሥልጣን የሰጣቸው እግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው ስሜት የፈለቀ አይደለምና ካህናቱም በጎቹን ሊመሩበት በጎች ምዕመናንም በካህናቱ ሊመሩበት ኦርቶዶክሳዊ ግዴታ ነው፡፡ )
- ካህናት የተሾሙት የበጎች ምዕመናንን ውስጣዊ ሕይወት ለመለካት ወይም ለመመዘን እንዲሁም እንደ ጥፋታቸው መጠን ለመቅጣትና ለማረም ነው፡፡ ይህንም ምዕመናኑ ሲናዘዙ ካህናቱ ቀኖና ሲሰጡ፣ ምዕመናኑም ቀኖናውን ሲፈጽሙት እንመለከተዋለን፡፡
- ካህናቱም የሚለኩት ወይም የሚመዘኑት በኤጲስ ቆጶሳት/ጳጳሳት/ሊቃነ ጳጳሳት ሲሆን እነርሱም በቅዱስ ፓትርያርክ በሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ይለካሉ(ይመዘናሉ) እነርሱም ሕግ አውጪ ናቸው፡፡ ቅዱስ ሲኖዶሱም በመንፈስ ቅዱስ ይለካል ይመዘናል፡፡
- እያንዳንዱ ምዕመን ቢያጠፋ የሚመረምረው ካህኑ ነው፡፡ መንፈሳዊነታችንን አስተካክሎ የሚያንጸው ካህን ነው፡፡ እነዚህም ካህናት የንስሐ አባት ይባላሉ፡፡ ሕግ አስፈጻሚዎች እነርሱ ናቸው፡፡ የሚጠሩትም ስለክህነታቸው ክብር አንቱ ተብለው ነው፡፡
- የንስሐ አባቶቻችን ይለኩናል፣ ይፈርዱብናል፣ ከበዛባቸው ያወግዙናል ይለዩናል፡፡ *__ገላ 3፡10፡፡__*
- ቀኖና (ሕግ) ቤተ ክርስቲያን በሁሉ ሲጠበቅ ሁሉ ሰላም ይሆናል፤ ሲጣስ ግን ችግር ነው፡፡ ሁሉ ራሱን እንደ ሕግ አውጪ (ሲኖዶስ) ወይም እንደ ሕግ አስፈጻሚ (ካህን) ከቆጠረ እንዲሁ ችግር ነው፡፡ እንዲህ የሚያደርጉ በእግዚአብሔርና በሰውም የመቀጣት (የመቀሰፍ) መከራን በራሳቸው ያመጣሉና - ቀኖና ቤተክርስቲያንን እናክብር፡፡

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org